## በችካጎና አካባቢዋ ለምንኖር ኢትዮጵያውያን በሙሉ የተላለፈ

APRIL 27-28 2013

## አስቸኳይ ብሄራዊ ጥሪ !

የኢትዮጵያና የአንድነቷ ፀር የሆነው የወያኔ ቡድን በለስ ቀንቶት በዋና ከተማችን በአዲስ አበባ ከከተመ ወዲህ ፥ የሀገራችንን ዘላቂ ጥቅምና ሰላም በእጅጉ ጎድቶታል። አሁንም ፥ ከምንጊዜውም በላይ በመጉዳት ላይ ነው ። በቅርቡ በኢትዮጵያውያን እስላሞችና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተውሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ላይ እያደረሰ ያለው ማፈናቀል ፥አፈና፥ እስራት ፥ ግድያና ጭፍጨፋ ተባብሷል ። ምንም እንኳን፥ ኢትዮጵያዊነት በአቸናፊነት እየዋጣ ቢሆንም፥ ይህ ጎጠኛ ቡድን ፥ ከነግብረ-አበሮቹ በአማራ ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለው የዘር ማጥፋት ተፋፋሟል ። በጉራ ፈርዳና በቤንሻንጉል ወዘተ በሽ የሚቆጠሩትን አፈናቅሏል ። ካፈናቀላቸውም በኋላ አሰቃቂ የአካል ጉዳትና የመንፈስ ስብራት እያደረሰባቸው ነው። ይህ ብሄራዊ ወንጀል መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አሳዝኖታል ። አስቆጥቶታለም ! የድርጅት መሪዎችና አባላት ፥ ጋዜጠኞችና ደራሲያን ፤ ሌሎች የነፃነት ተዋጊዎች የሃይማኖት መሪዎች፤ የሰበዓዊ መብቶች መጣስ ተቆርቋሪዎች ፥ የወያኔን ወኅኒ ቤቶች አጨናንቀዋል። በርካታ ዕንቁ የኢትዮጵያ ዜጎች የት እንደደረሱ አይታወቅም። ወያኔና ግብረ-አበሮቹ፥ ከራሳቸው አልፈው-ተርፈው፥ ቤተሰቦቻቸውንና የጎሳቸውን አባላት እያበለፀጉ ይገኛሉ። በመሆኑም ፥ የገሪቱን አንጡራ ሀብት ከመቀራመታቸውም በላይ፥ ከውጭ የሚገኘውን ርዳታና ብድር ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ወደ ውጭ አሸሽተዋል ። ስለዚህ የውጭ ምንዛሬ ዕጥረት ስለደረሰባቸው፥ ሁለተኛ ዙር የዐባይ ቦንድ ሽያጭ በሚል ስም ፥ ዐይን ያወጣ ዘረፋ እያካሄዱ ይገኛሉ ። ግን በየቦታው ከፍተኛ ተቃውሞና ውርደት እየተካሄደባቸው ነው ። በችካጎ ከተማም አምባሰዳር ተብየው ግርማ ብሩ የተሰኘውን ግለሰብ በ4-27- 13 እና በ4- 28-13 ለማስመጣት ቅጥረኞቹ ሽብ-ረብ እያሉ ናቸው። ይም ይከሽፋል! ለመሆኑ ፥ የዐባይ ግድብ አገልግሎቱ 51 ከመቶ የውጭ መንግሥታት ድርሻ መሆኑንና 49 ከመቶ የወያኔ ድርጅት የሆነው ኤፈርት መሆነን ያውቃሉን ? ይህን የወያኔን ቆርፋዳ ውሸት አናርጥብ ! ሰሚ ጆሮና አስተዋይ አዕምሮ ይኑረን ! ይህንን አገረ-በቀል ጠላት ከሕዝባችን ጫንቃ ላይ ለማስወገድ በቁርጠኝነት እንነሳ ! የወያኔ መጠንከር፥ የኛ መፋዘዝ ነውና እየሞተ ያለው ወያኔ መቀበሪያ ጉድጓዱን እየቆፈረ ስለሆነ ከመቀበሪያው ጉድጓድ ለማድረስ ገንዘብ መስጠት ሳይሆን፥ መስራት ያለብን፥ ቃሬዛውን ማዘጋጀት ብቻ ነው !

አንድነታችን በእኩልነት ላይ በተገነባ ኃይል ይጠነክራል !!!
የኢትዮጵያ ነፃነትና ትንሣዔ በወያኔ ከርሰ- መቀር ላይ ያብባል !!!

እናት አገራችን ኢትዮጵያ በአንድነቷና በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኖራለች!!!

የኢትዮጵያ አምላክ አገራችንና ሕዝቧን ይጠብቅልን !!!